## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# በሆላንድ ዩትሬክት ከተማ የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የቀረበ ሰነድ

## 1. መግቢያ፤

በግንቦት 97 ምርጫ ህዝባችን አንደኛ በነቂስ ወጥቶ ተሳትፎ በማድረጉ፤ ሁለተኛ የኢህአዴግ መሪዎችን በምንም አይነት በማያወላዳ ሁኔታ በዝረራ አሸንፎ የመንግስት ለውጥ እንዲደረግ በመወሰኑ፤ ሶስተኛ ደግሞ ይህንን በመስዋእትነቴ ያገኘሁትን ድሌን በጠራራ ፀሃይ አልነጠቅም ብሎ ከነዚህ ጥቂቶች ጋር እልህ በተጋባ መልክ ትንንቅ በመያዙ በፖለቲካ ያገባናል ለሚሉ ሃይሎች በማስተላለፍ ላይ ያለው መልእክት ለማንኛችንም ብዙ አማራጭ የሚተው መልእክት አይደለም።

ለኢህአዴግ መሪዎች ያቀረበላቸው ምርጫ ሽንፈትን በፀጋ ተቀብለው በቀረበላቸው የብሄራዊ እርቅ ሃሳብ መስማማት ወይም ደግሞ በለየለት ሸብር ተሰማርቶ አገር ለመግዛት መሞከር የሚል ምርጫ ነው። ይህንን ሁለተኛውንና አደገኛ የሆነውን አካሄድ ከመረጡ ተጨማሪ ዴሞክራሲ ቀርቶ ከእንግዲህ ላለፉት አስራ አምስት አመታት ሲመፃደቁበት የቆዩትን የዴሞክራሲ ፍንጭ እንኳን ለማረጋገጥ የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አይሆኑም። ድሮውንም ቢሆን ሳይደላደል በአንድ እግሩ ቆሞ የነበረው ነፃ ፕሬስ ዛሬ ያለበትን ሁኔታ ስናይ፤ ከሰኔ ወር ወዲህ ያለአንዳች ተጠያቂነት የፈሰሰውንና በመፍሰስ ላይ ያለውን ደምና በህዝባችን ላይ የተፈፀመውንና በመፈፀም ላይ ያለውን ዘግናኝ ግፍ ስንታዘብ፤ በአጠቃላይ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ሃገራችን ከአንድ አመት ወዲህ የዘቀቀችበትን ደረጃ ስንመለከት የምንደርስበት መደምደሚያ አንድና አንድ ብቻ ነው። በዚህ ፀረ ህዝብ ምርጫው የተነሳ የኢህአዴግ መሪዎች ሃገራችንን፤ ህዝባችንን፤ አባሎቻውንን ደጋፊዎቻቸውን ይዘው ወደ ጥፋት እየነጎዱ መሆናቸው ግልፅ ነው።

በትግል ላይ ያለው ህዝባችን ለሃገራችን ዴሞክራቶች ያቀረበላቸው አማራጭም የዚያኑ ያህል ግልፅ ነው። የመጀመሪያው አማራጭ ህዝቡ አጀንዳየ ብሎ የሚንቀሳቀስበትን የድምፄ ይከበር አጀንዳ ሳይሸራርፉ መቀበል፤ የትግሉ ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ ራሱ በማካሄድ ላይ ያለውን ተጋድሎ በጥቂቶች የድርድር ሂደት እንተተካለን ብሎ አጉል ሳይግደረደሩ ከህዝቡ ትግል መደባለቅ፤ በዚህ ተጋድሎው ከሚከፍለው መስዋእትነት የሚመጥን ፍሬ እንዲያገኝ ጥራት ፤ ተአማኒነትና ተጨባጭነት ያለው አመራር ሰጥቶ ለድል ማብቃት ነው። አማራጭ ብሎ መጥራት አግባብአይኖረውም እንጂ ከዚህ ውጭ ያለው አካሄድ የዴሞክራታይዜሽኑን ሂደት መቀልበስ አሜን ብሎ ተቀብሎ፤ ለሽብር አገዛዝ ተንበርክኮ፤ ህዝብን አውላላ ሜዳ ላይ በትኖና አጋፍጦ ከታሪክ መድረክ ተዋርዶ የመውረድ አማራጭ ነው። ይህ ደግሞ የህዝባችን የዴሞክራታይዜሽን ተጋድሎ ምናልባት ለአንድ ትውልድ የሚተላለፍበት ዘግናኝ ሁኔታ እንዲሰፍን የሚያደርግ መዘዘኛ አካሄድ በመሆኑ ህብረታችን እንኳን ሊመርጠው ሊያስበውም ይቀፈዋል።

ባጭሩ ሃገራችን ወይ ከህዝባዊ ድል ወይ ከሽብር ሌላ መፈናፈኛ በማይሰጥ ታሪካዊ ወቅት ውስጥ ተገኛለች። በኛ ግምት ሃገራችን ከዚህ አጣብቂኝ ልትወጣና ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ልትሸጋገር የምትችለው ዛሬ በትግል ላይ የምንገኝ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከአለፉት የኪሳራ የሽግግር ሂደቶች ትምህርት ቀስመንና ዛሬ ያለውን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር የተመቻቸ ሁኔታ ተገንዝበን የትግል ስትራቴጂ በማውጣት ነው።

## 2. ካለፉት የሽግግር ሂደቶች ስለመማር፤

የአለፉት የሽግግር ሂደቶች ለኪሳራ የበቁት ለስልጣን ተቀናቃኝ የነበሩት ሃይሎች ለህዝባችን እንደለፈፉት ትኩረታቸው ህብረተሰባችንን "ከማሸጋገር" ይልቅ የሽግግሩን ሂደት አንድ ድርጅት ወይም የድርጅቶች ስብስብ ሌላን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ስብስብ የሚተካበት ተራ የስልጣን ዝውውር ወይም ቅብብሎሽ ተጋድሎ አድርገው በመውሰዳቸው ነበር። የኢትዮድያ ዴሞክራቶች ቢያንስ በእይታ ደረጃ ከእንዲህ አይነቱ ጠባብ አመለካከት የራቀ የሽግግር ሂደት ሲያራምዱ ረዥም ጊዜ ሆኗቸዋል። የዛሬ አስራ ሶስት አመት የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች ራሳቸውን ከሽግግር ወደ ቋሚ መንግስትነት ለመቀየር ላይ ታች ሲሉ ዛሬ በህብረቱ ውስጥ ተካትተው የሚገኙ ታጋዮችና የኦነግ ወገኖቻችን ተወካዮችም በተገኙበት በፓሪስ አንድ ጉባኤ ላይ ተማምነን ያፀደቅነውና በጋራ ሰነዳችን ያሰፈርነው መሰረታዊ አቋም

*" ዛሬ ኢትዮድያ የሚያስፈልጋትና ህዝቦቿም በጉጉት የሚጠብቁት ሽግግር አንድ መንግስት ሌላውን የሚተካበት ወይም አንድ የፖለቲካ ሃይል በሌላ የሚለወጥበት ወይም ደግሞ አንድ ጊዜያዊ መንግስት ወደ ቋሚነት የሚሸጋገርበት ሂደት ብቻ አይደለም። የሚያስፈልገን ህብረተሰቡ በሙሉ ከአንድ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ወደ ተሻለና የመላውን ህዝብ ተቀባይነት ወደ አገኘ ስርአት የምንሄድበት ሽግግር ነው።"* በማለት የጋራና ትክክለኛ እይታችንን ለኢትዮድያ ህዝብ አብስረናል።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ በሽግግር ስም ሃገራችን በወያኔ/ኢህአዴግ አስከፊ አገዛዝ ስር ወደቀች። ለዚህ የኪሳራ ሂደት የነዚህ ፀረ ህዝብ ሃይሎች ለእንዲህ አይነቱ በጎ አካሄድ ብቃት ማነስና የባእዳን ሃያላን ጣልቃ ገብነት እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ቢችሉም በኛ ግምት እነዚህ በቂ አይደሉም። ከንጉሳዊ አገዛዝ ወደ ደርግ፤ ከደርግ አገዛዝ ወደ ኢህአደግ የተደረጉት ሽግግሮች ለህዝባችን የኪሳራ ሂደቶች ሆነው ለመክሰም የበቁት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በምንመኘው መልክ ህብረተሰባችን ራሱን በራሱ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር የሚያስችሉት ተቋሞችና እይታዎችም ሆኑ የፖለቲካና የስነልቡና ሁኔታዎች ተሟልተው ባለመገኘታቸው ነበር።

## 3. ያለንበት ለሽግግር አመች ሁኔታ፤

ባለፊት አስራ አምስት አመታት ከእነዚህ አንፃር ይህ ነው የማይባሉ በጎ ለውጦች በመካሄዳቸው የተነሳ ዛሬ በቀደሙት ሁለት የኪሳራ ሂደቶች ያልነበሩና የምንመኘውን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ለትግላችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚችሉ አዳዲስ ክስተቶች አሉ። መዋቅራቸውን በህቡእ ዘርግተው በሃገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ በህግ ታውቀው ሚልዮኖችን ለማንቀሳቀስ ብቃት ያላቸው ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ከነዚህ በተጨማሪ ትግላቸውን በቀጥታ ከፖለቲካ ጋር ሳያያይዙ ለሃገርና ለወገን፤ ለመብ-ት፤ ለሙያና ለህጋዊ ጥቅም እንዲሁም ለባህላዊ ህልውናና ለመሳሰሉት አላማዎች የሚንቀሳቀሱ ስብስቦች እንደ አሸን ፈልተዋል። እየደማና እየተዋከበም ቢሆን ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ለመዳበር የሚሞክረው ነፃ ፕሬስ ህብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለመቀስቀስና ለማዘጋጀት ባደረገው ጥረት አዳዲስና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች በሃገራችን እንዲሰርፁ ተደርጓል። በቀደሙት ሽግግሮች ካልነበሩት በጎ ክስተቶች አንዱ ዛሬ በውጭ አገሮች ለህዝባችን የዴሞክራሲ ትግል በሃሳብ፤ በማቴርያል፤ በዲፕሎማሲ መስክ ተሰማርተው የሚዋደቁ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች አሉ። በነዚሁ ወገኖች ብርታት በዚሁ በዲፕሎማሲው- መስክ የኢህአዴግ መንግስት ለአለፉት አስራ አምስት አመታት አጥልቆት የነበረው የዴሞክራሲ ካባ ተገፎ ዛሬ እርቃኑን የቆመበት በዚያው ልክ ደግሞ በታሪካችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የህዝባችን የዴሞክራሲና የፍትህ ተጋድሎ አለም አቀፍ ድጋፍ ያገኘበት ወቅት ውስጥ ነን።

በነዚህና በመሳሰሉ ሌሎች በታሪካችን ያልነበሩ አዳዲስ ክስተቶች ሳቢያ ዛሬ ቀደም ሲል የነበረው ክፍተት ተደፍኖ ህብረተሰባችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ከመቸውም ይበልጥ የተመቻቸበት ሁኔታ ውስጥ ይ ገኛል። በዚህም የተነሳ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ህብረተሰባችን እንዴትና ወዴት ለመሄድ እንደሚፈልግ የሚያውቅ፤ በየደረጃው ከአብራኩ በፈለቁና በሚቆጣጠራቸው ተቋማትና ሃይሎች ራሱን በራሱ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ለማሸጋገር የሚችልበት የታሪክ ምእራፍ ላይ ይገኛል የሚል ፅኑ እምነት አለን። የግንቦት 97 ምርጫ በሂደቱም ሆነ በውጤቱ በእነዚህ ባለፉት አስራ አምስት አመታት በተካሄዱት ትግሎችና በተከፈለው መስዋእትነት አማካኝነት ቀስ በቀስ በዳበሩት ድሎች ሳቢያ የደረስንበት ታሪካዊ ምእራፍ ነው።

## 4. እነዚህን ድሎች ለመደምሰስ ወይም ለማጎልበት ስለተያዘው ታሪካዊ ትግል፤

ዛሬ በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚደረገው ታሪካዊ ትግል ማንም የፖለቲካ ሆነ ሌላ ስብስ ብ የሚያወጣው ስትራቴጂ በአጥፊም ሆነ በአልሚነት የሚመዘነው ከእነዚህ ድሎች አንፃር በሚወስደው አቋ ም ብቻ ነው።

ከዚህ አንፃር ሲታይ የኢህአዴግ መሪዎች አካሄድ ግልፅ ነው። ህልማቸው የህዝብ ድምፅ ሰርቆ ለሌ ላ አምስት አመታት በስልጣን ለመቆየት ብቻ የሚጥር ህልም አይደለም። ዛሬ በአይናችን ስር እየተካሄደ ከአ ለው ዘግናኝ የሽብር ውርጅብኝ ባሻገር ሙከራቸው ህብረተሰባችን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር ብቁ ያደረጉትን በ መስዋእትነት የተገነቡትን እነዚህን ተቋማት በማፈራረስና በህዝባችን ልቡና የሰረፁትን በጎ የአስተሳሰብ ለው ጦች በማውደም የዛሬ ሃያም ሰላሳም አመት የነበረውን "የሽግግር ክፍተት" መልሶ እውን ለማድረግ የሚጥር መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ ነው።

በህብረታችን እምነት ዛሬ የዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ሃይሎች ዋናና አንገብጋቢ ተግባር የኢህአዴግ መሪዎች በዚህ መልክ ለማዝረክረክና ለማውደም የሚሞክሯቸውን እነዚህን የህብረተሰባችን ድሎች በህዝባዊ ትግል አስመልሶ መንከባከብና በነሱ ላይ እየገነቡ ወደ ፊት የመራመድ አደራ ነው። ማስመለስ፤ መንከባከብ ፤ በነሱ ላይ መገንባት። ዛሬ ባለንበት የሽብር አገዛዝ ስር ሶስቱ አላማዎች በአንድ የህዝባዊ ተጋድሎ ሂደት የ ሚረጋገጡ እንጂ ተነጣጥለው የሚታዩበት ምንም ተአምር አይኖርም። መሪዎቻችንንና ሌሎች በሽህ የሚቆጠ ሩ ታጋዮችን ከእስር ማስፈታት፤ የነፃው ፕሬስ ባልደረቦች በሙሉ ተለቀው የህዝብ ድምፅ ሚናቸውን እንዲቀ ጥሉ መሟገት፤ በህዝባችን ልይ ለተፈፀሙት ግፎች ሁሉ ተጠያቂነትን መጠየቅ የህዝቡን ድሎች ለማስመለስ የሚካሄዱ ተጋድሎዎች ናቸው። ነገር ግን በዚሁ የትግል ሂደት ገፍተን ዴሞክራሲ፤ የህግ የበላይነት፤ ተጠያ ቂነት የሚሰፍኑበት በህዝባዊ ስርአት ካልቋጠርናቸው የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት እስካለ ድረስ ነገሩ ሁሉ ው ሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆናል። ተመልሰው ይነጠቃሉ። ባጭሩ ለማስቀመጥ ድሎቻችንን አስመልሰን ወደ ዴሞ ክራሲያዊና የተረጋጋ ስርአት በሚደረገው ትግል ሳያቋርጡ መታገል ጊዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ሃላፊነት ነ ው።

## 5. የትግሉ አላማና የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪካዊ ሚና፤

ካለፉት ሂደቶች ተምረን ወደ ፊት እንራመድ ካልን ከወዲሁ መቀበል ያለብን መሰረታዊ ሃቅ አለ። ህብረተሰባችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሸጋገር በሚደረገው ትግል የፖለቲካ ድርጅቶች ወሳኝ የግንባ ር ቀደም ሚና ቢኖራቸውም የተጋድሎው አልፋና ኦሜጋ እነሱን ብቻ አድርጎ መቁጠር ሌላ ታሪካዊ ስህተት ይሆናል። " እየታገልን ነው፤ ተጋግዘን ተባብረንና ስልጣን ይዘን ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ይደረጋል" የሚለው አካሄድ አያዋጣም። ለህዝባችን የሚበጀው ሽግግሩ በማንም ይሁን በማን ራሱን "የሽግግር መንግስት" ብሎ በ

ሚጠራ ድርጅት ወይም ስብስብ ሳይሆን በጠቅላላው በህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ተሳትፎና አመራር የሚካሄድ ሂደት ሆኖ ከታየ ብቻ ነው።

ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ መጀመሪያ በህዝባዊ ትግል ኢህአዴግን አስገድዶ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች፤ የወጣቶችና የሴቶች፤ የሰራተኞችና የገበሬዎች፤ የነጋዴዎች፤ የጋዜጠኞች፤ የሙያ፤ የጥቅም፤ የባህል፤ የምሁራንና የባለሙያዎች ማህበራትና ስብስቦች ተወካዮች፤ የሃይማኖት መሪዎችና የሃገር ሽማግሎች፤ እንዲሁም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች የሚሳተፉበት ሰፊ አገር አቀፍ ጉባኤ ተጠርቶ የዴሞክራሲውንና የሽግግሩን ሂደት መልክ የሚያስይዝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መስራት ይኖርብናል። ሁለተኛ የሽግግሩ ዋና ባለቤት መን-ግስት ሳይሆን ህብረተሰቡ ስለሚሆን ይህ ጉባኤ ህብረታችን ባቀረበው አማራጭ ፕሮግራም በሰፊው በአብራራው መሰረት በአንድ በኩል የዴሞክራታይዜሽን ኮሚሽን በሌላ በኩል ደግሞ የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን በመሰየም በነዚህ ተቋማት አማካኝነት ሽግግሩን ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

6. <u>ወደዚህ ህዝባዊ አላማ ለመድረስ ስለሚደረገው ትግል፤</u>

ሽግግሩ ለፖለቲካ ድርጅቶች እንደማይተው ሁሉ ወደዚህ አገር አቀፍ ጉባኤ የሚደረገውና የኢህአዴግን በህዝብ ትግል መሸነፍ የግድ የሚል አላማም ቢሆን በፖለቲካ ሃይሎች ተጋድሎ ብቻ የሚሳካ ተደርጎ መታየት የለበትም። ከፖለቲካው መስክ ውጭ ያለው ህብረተሰብም ቢሆን ከዚህ ከምንመኘው አገር አቀፍ ጉባኤ ''በተጋባዥነት'' የሚመጣ ሃይል ሳይሆን ይህ አላማ እንዲሳካ በሚደረገው ትግል ከወዲሁ በተራ ተሳትፎም ሆነ በአመራር ደረጃ ያገባኛል ብሎ በመግባት የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ሁለገብ ተሳትፎ እውን እንዲሆንና ትግላችን ለድል እንዲበቃ ዛሬ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ ያለው ማህበረ ሰብ ከሽግግሩ ባሻገር ነፃ ምርጫ እውን ሲሆን በህዝብ ፊት ይዘን በምንቀርባው ወገናዊ የፖለቲካ ፕሮግራሞች ዙሪያ ''የድጋፍ ኮሚቴ'' እያለ በአጋዥነት ከመሰለፍ አልፎ ''ቀድሞ ባሉን'' እንዲሉ መጀመሪያ የሁሉም ወገኖች የጋራ አላማ ለሆነው ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር በአንድ ሆኖ መታገል ይኖርበታል።

በኛ እምነት ከአለንበት የትግል ምእራፍ አንድ እርምጃ ተራምደን በኢትዮጵያ ምድር ሰፊና አገር አቀፍ የሽግግር ጉባኤ ለመጥራት እንድንችል ዛሬ በውጭ አገር ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የህብረተሰቡ ሃይሎች የተቻለውን ያህል የሚሳተፉበት ጉባኤ አዘጋጅቶ ትግሉን ሁሉን አቀፍ ማድረግ የማይታለፍ የግንባር ቀደም ሃይሎች ታሪካዊ ሃላፊነት ነው።

7. <u>በቀጣዩ ትግል የኡትሬክቱ ስብሰባ ስለሚኖረው ሚና፤</u>

በኛ ግምት ይህ ስብሰባ በውጭ አገር ስለሚያስፈልገን ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ለመምከርና ከዚህ አንፃር አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ለማቀድ ቅድመ ዝግጅት (ፕሬሊሚናሪ) ስብሰባ መሆን ስለሚኖርበት ከዚህ አንፃር እንዲታይ ሃሳብ እናቀርባለን። በዚህ ስብሰባ ላይ በአጠቃላይ ስለሽግግሩ ሂደት የጋራ ግንዛቤ የሚያደርሰን ውይይት ብናካሂድና በቀጣዩ ጉባኤ ስለሚሳተፉ ሃይሎች፤ ስለአጀንዳው ወዘተ ምክክር ተደርጎ ውሳኔ ላይ ቢደረስ ይህንን እውን ለማድረግ የሚሰራ አንድ የቀውጢ ጊዜ ኮሚቴ ማቋቋም ቢቻል ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብለን እንገምታለን።

ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.